

ጸሎተ ንድራ

፩. **አንድ አምላክ በሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ መለኮት** ባርያና(የሚጥል አጋንንትን) ሌጌዎንን፣ ኤድስና ካንሰርን፣ ምትሐትና ፍልጸትን፣ መጋኛና ውጋትን፣ ንዴድና ቡዳን፣ መሠርያን ርኩሳን መናፍስት ሁሉ ከኔ ይርቁ ዘንድ አወግዛቸዋለሁ። አምላኬ **ኢየሱስ ክርስቶስ** ጌታዬ ሆይ ሕይወቴን ጠበቅ ኃጢአቴንም ይቅር በል ። ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ እኔን ባርያህን .....ን አድኅኝ። ለዓለመ ዓለም አሜን!!!

፪. አንድ አምላክ በሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ፣ የንድራ ጸሎት ከ12ቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥብርያዶስ ባሕር ሲሄድ መልኳ አዛውንት የምትመስል ሴት ከዛፍ ሥር ተቀምጣ ተመለከቱ። እርሷም እጅግ ታስፈራና ታስደነግጥ ነበር። ዓይኖቿም እንደ ቀይ ወርቅ ያብረቀርቃሉና ፤ እጆቿና እግሮቿም እንደ እሳት ሠረገላ ናቸው። በመልአኩ ክንድ 807 ያክል ከአፏም እንደ እሳት ነበልባል ይወጣ ነበር።

፫. ደቀ መዛሙርቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይህች የተረገመች ዓይነ ክፉ ምንድን ናት አሉት።ፈረስ እየሮጠ ባየች

ጊዜም ከተጫነው ጋር በፍጥነት ጥላዋለችና።

፬. በባሕር ላይ የሚሄድ መርከብ ባዮችም ጊዜ በፍጥነት ገለበጠችው። የምትታለብ ላምንም ባዮች ጊዜ ወተቷ ደም ይሆን ፈጽሞም ይኦጥፍ ነበር። ባልና ሚስትን ከልጆቻቸው ጋር፤ ሾማሌና አሮጊት ባዮች ጊዜ ፈጥና ታለያያቸዋለች ፤ፈጽማም ታጠፋቸዋለች።

፭. የጌታችን ደቀ መዛሙርትም ይቺን ዓይነ ክፉ የተረገመች በምን እናጠፋታለን አሉት። ጌታችንም ለሐዋርያት እንዲህ አላቸው የማይነገር የማይተረጎም ድንቅ ስሞቼን እንኩ

ሰጠኋችሁ። በእሳት አቃጥሏት፤ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ የስም አጠራሯ እንዲጠፋ በነፋስ በትኗት።

፮. ከዚህም ቦኋላ 12ቱ ደቀ መዛሙርት ቅዱሳት የሆኑ ስሞቹን ወሰዱ። እንደዚህ እያሉም በመስቀል ምልክት አማተቡ።

በትረኮን፤ አትረኮን፤ አትረኮን፤ በትረኮን፤ በትረኮን፤ በትረኮን፤ አተርጋሞን፤ አተርጋሞን፤ አተርጋሞን፤ አተርጋሞን፤ አዊል፤ አዊል፤ አዊል፤ ሚሎስ፤ ሚሎስ፤ ሚሎስ፤ ጋዲን፤ ጋዲን፤ ጋዲን፤ ብርስባሔል፤ ብርስባሔል፤ ብርስባሔል፤ ጴቃ፤ ጴቃ፤ ጴቃ፤ ሴቃ፤ ሴቃ፤ ሴቃ፤ ቤቃ፤ ቤቃ፤ ቤቃ፤ የጡለ፤ ቀርንው፤ ቀርንለው፤ አማኑኤል፤ ኢያኤል፤ ክስብኤል፤ ክስብኤል፤

ክስብኤል፣ አካዕ፣ አካዕ፣ አካዕ፣ አህያ፣ ሸራህያ፣ ኤልሻዳይ፣ እልመሳኩን፣ ጸባኦት፣

፮. አንድ አምላክ በሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስሞች አሌፍ፣ ቤት፣ ጋሜል፣ ዳሌጥ፣ ሄ፣ ዋው፣ ዛይ፣ ሄት፣ ጤት፣ ዮድ፣ ካፍ፣ ላሜድ፣ ሜም፣ ኖን፣ ሳምኬት፣ ዔ፣ ፌ፣ ጻዴ፣ ቆፍ፣ ሬስ፣ ሳን፣ ታው አቤቱ አምላኬ ልመናዬ ወዳንተ ትድረስ በእነዚህ የስሞችህ ኃይል ከምፈራው ክፉ ነገር ሁሉ እኔን.....ን አድኑኝ።

፯. ከዓይን ሕመም ጀምሮ የሚጥል በሽታ፤ ርኩሳን መናፍስትና ጸዋጋን አጋንንት፣ ቡዳና እጀ ሰብእ፣ ዓይነ ወግና የሥጋ ደዌ ወደ ሥጋና ነፍሴ እንዳይቀርቡ በአብ

እታመናለሁ በወልድ እጠለላለሁ በመንፈስ ቅዱስ እከለላለሁ ሳዶር፣ አላዶር፣ ዳናት፣ አዴራ፣ ሮዳስ በእነዚህ በአምስቱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀሉ ችንካሮች ከምፈራው ክፉ ነገር ሁሉ እኔን .....ን አድነኝ።

፱. ቃል ሥጋ ሆነ በኛ ላይም አደረ። የእግዚአብሔር ቃል እንደ እሳት ያቃጥላል። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። ያ ቃል ቀዳማዊ ነው ያ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፤ ያም ቃል እግዚአብሔር ነው።

፲. እንዲሁም ቀዳማዊ ቃል አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። በእርሱም

ሁሉ ተፈጠረ። ከተፈጠረው ሁሉ ያለ እርሱ ግን ምንም የተፈጠረ የለም። እርሱን ለማገልገል የተፈጠረው ሁሉ በእርሱ ስልጣን የተፈጠረ ነው ፤ ሕይወትም ነው ፤ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነው። ብርሃንም በጨለማ ውስጥ ያበራል፣ ያሳያል ፤ ጨለማም አይቀርበውም፣ አያገኘውም።

፲፩. ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በዚህ የወንጌልህ ቃል እኔን ባርያህን.....ን ከምፈራው ክፉ ነገር ሁሉ አድነኝ።

፲፪. አንድ አምላክ ቦሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ስለ ነፍስና ሥጋ በሽታ ጸሎት። በሰማይ አንተ ነህ። በምድርም አንተ

ነህ። አንተ ታድናለህ ፣ አንተም ትገድላለህ። ፈጽሞ እንቅልፍ የለህም። አንተ የሰማያትና የምድር ንጉሥ ነህ።

፲፫. ከእጅና ከእግር ውስጥ ያለ ፤ ከሆድ ውስጥና ከልብ ውስጥ ያለ ፤ በጎሊና ውስጥ ያለ ፤ አንተ ታውቃለህ በእጅህ ውስጥ አጽናን። በሰማያት ውስጥ ያለህ ሁሉን የምትሰማ እግዚአብሔር አንተ ነህ። ፈጽሞ ጽኑዕ እና ኃያል እግዚአብሔር አንተ ነህ።

፲፬. ከግራና ከቀኝ፤ ከፊትና ከኋላ ከሚመጡ ሰይጣናትና ከማይመጡ ክፉ ሰዎች ሁሉ አድኑኝ። አንተ እግዚአብሔር ታውቃለህ እግዚአብሔር ሆይ አዋቂ

አንተ ብቻ ነህ። ቅሩብ በሆነ በእግዚአብሔርና ስለክርስቶስ እናት ስለ እመቤታችን ማርያም አንተ ርኩስ መንፈስ ከእግዚአብሔር ባርያ ከ..... ላይ ውጣ።

መዝሙር 18

ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ
የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል
ቀኒቱ ለቀን ነገርን ታወጣለች
ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች
ነገር የለም መናገርም የለም ድምጻቸውም አይሰማም
ድምጻቸው በምድር ላይ ተሰማ
ቃላቸውም ሁሉ እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ

በእነርሱም ውስጥ የፀሐይን ድንኳን አደረገ።

እርሱም እንደ ሙሽራ ከእልፍኙ ይወጣል።

እንደ አርበኛ በመንገዱ ለመሮጥ ደስ ይላል።

አወጣጡ ከሰማያት ዳርቻ ነው።

ሂደቱም እስከ ዳርቻቸው ነው።

ከዋዕይነቱም የሚሰወር የለም።

የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው ነፍስን ይመልሳል።

የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው።

ሕፃናትን አዋቂዎች ያደርጋል።

የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው ልብን ደስ ያሰኛል።

የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው ዐይንንም ያበራል።
እግዚአብሔርን መፍራት ንጹሕነት ነው ለዘለዓለም ያኖራል።
የእግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅንነት በአንድነት ነው።
ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል
ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል።
ባርያህ ደግሞ ይጠብቀዋል።
በመጠበቁም እጅግ ይጠቀማል።
ስሕተትን ማን ያስታውሳታል።
ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ።
የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዙኝ ባርያህን ጠብቅ።
የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ።

ከታላቁም ኃጢአት እነፃለሁ።

አቤቱ ረድኤቴ መድኃኒቴም

የአፌ አነጋገር የልቤም አሳብ

በፊትህ ያማረ የተወደደ ይሁን ።

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
አስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን።

መዝሙር 90

በልዑል መጠጊያ የሚኖር።

ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ

ያድራል።

እግዚአብሔርን አንተ መታመኛዬ

ነህ እለዋለሁ።

አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው በእርሱም

እታመናለሁ።

እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ

ከሚያስደነግጥም ወጥመድ ያድንሃልና።
በላባዎቹ ይጋርድሃል።
በክንፎቹም ጥላ ትጠለላለህ።
እውነት እንደ ጋሻ ይከብሃል።
ከሌሊት ግርማ በቀን ከሚበር ፍላጻ
በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር
ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም።
በአጠገብህም ሺህ በቀኝህም ዐሥር
ሺህ ይወድቃሉ።
ወደ አንተ ግን አይቀርቡም።
በዓይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ።
የኃጥአንንም ብድራት ታያለህ።
አቤቱ አንተ ተስፋዬ ነህና።
ልዑልን መጠጊያህ አደረግህ።
ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም።

መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም::
በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ
መላእክቱንስለ አንተ ያዛቸዋልና::
እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል
በእጆቻቸው ያነሡሃል::
በተኩላና በእባብ ላይ ትጫማለህ::
ዘንዶውንና አንበሳውንም ትረግጣለህ
በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ::
ስሜንም አውቋልና እጋርደዋለሁ::
ይጠራኛል እመልስለትማለሁ::
በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ
እሆናለሁ::
አድነዋለሁ አከብረውማለሁ::
ረጅም እድሜ እሰጠዋለሁ::
ማዳኔንም አሳየዋለሁ::

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
አስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን።

መዝሙር 26

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነውና
የሚያስፈራኝ ምንድን ነው?
እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ
ነውና የሚያስደነግጠኝ ምንድር ነው?
ክፉዎች አስጨናቂዎች ጠላቶቼም
ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ በቀረቡ ጊዜ
እነርሱ ተሰናክለው ወደቁ።
ጠላትም ቢከበኝ ልቤ አይፈራም።
ሰልፍም ቢነሳብኝ በዚህ እተማመናለሁ።
እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት
እርስዋንም እሻለሁ በሕይወቴ ዘመን
ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ

ማረኝ አድምጠኝም::
አንተ ፊቴን እሹት ብለኻልና አቤቱ
ፊትህ እሻለሁ ልቤም አንተን አንተን
አለ::
ፊትህን ከእኔ አታዙር::
ተቆጥተህ ከባርያህ ፈቀቅ አትበል::
ረዳት ሁነኝ አትጣለኝም::
የመድኃኒቴም አምላክ ሆይ አትተወኝ::
አባቴና እናቴ ጥለውኝ ነበርና::
እግዚአብሔር ግን ተቀበለኝ::
አቤቱ መንገድህን አስተምረኝ::
የሐሰት ምስክሮችና ዓመፀኞች
ተነሥተውብኛልና::
ለጠላቶቼ ፈቃድ አሳልፈህ አትስጠኝ::
የእግዚአብሔርን ቸርነት በሕያዋን

እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን አይ ዘንድ።

መቅደሱንም እመለከት ዘንድ ነው።

በመከራዬ ቀን በድንኳኑ ሰውሮኛልና።

በድንኳኑም መሸሸጊያ ሸሽጎኛልና።

በአደባባይም ከፍ ከፍ አድርጎኛልና

እነሆ አሁን በዙሪያ ባሉ በጠላቶቼ ላይ ራሴን ከፍ ከፍ አደረገ።

በድንኳኑም የምስጋና መሥዋዕትን ሠዋሁ።

ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ እዘምርለትማለሁ

አቤቱ ወደ አንተ የጮኩትን ቃሌን ስማኝ

ምድር አይ ዘንድ አምናለሁ።
እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ
በርታ ልብህም ይጽና።
እግዚአብሔርን ተስፋ እናድርግ።

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
አስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን።።

መዝሙር 55

አቤቱ ሰው ረግጦኛልና ማረኝ
ሁልጊዜም በሰልፍ አስጨንቆኛል።
የሚዋጉኝ በዝተዋልና።
ሁልጊዜ ቀኑን ሁሉ ጠላቶቼ ረገጡኝ
እኔ ግን ፈራሁ በአንተም ታመንሁ።
በእግዚአብሔር ታምኜ ቃሉን አመሰግናለሁ

በእግዚአብሔር ታምኖለሁና አልፈራም
ሰው ምን ያደርገኛል
ሁል ጊዜ ቃሉቼን ያጸይፉብኛል::
በእኔ ላይም የሚመክሩት ሁሉ ለክፉ
ነው::
ይሸምቁብኛል ይሸሸጉብኝማል::
እነርሱም ፍለጋዬን ይከታተላሉ::
ሁልጊዜም ነፍሴን ይሸምቁባታል::
በምንም በምን አታድናቸውም::
አሕዛብን በቁጣ ትጥላቸዋለህ::
አምላክ ሆይ ሕይወቴን ነገርሁህ::
እንባዬን እንደ ትእዛዝህ በፊትህ አኖርህ
በጠራሁህ ጊዜ ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው
ይመለሳሉ::
በዚህም አንተ አምላኬ እንደሆንህ እነሆ

እነሆ አወቅሁ።

እግዚአብሔርን ታምኜ ቃሉን አመሰግናለሁ

እግዚአብሔርን ታምኜ ሕጉን አከብራለሁ

እግዚአብሔርን ታመንሁ አልፈራም

ሰው ምን ያደርገኛል።

አቤቱ የምስጋና ስእለት የምሰጥህ ከእኔ ዘንድ ነው።

ነፍሴን ከሞት እግሮቼን ከመውደቅ አድነሃልና።

በሕያዋን ብርሃን እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው ዘንድ።

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን።

መዝሙር 139

አቤቱ ከክፉ ሰው አድነኝ።

በልባቸው ክፉ ከአሰቡ

ከዓመፀኞች ሰዎች ጠበቀኝ።
ቀኑን ሁሉ ለሰልፍ ይከማቻሉ።
ምላሳቸውን እንደ እባብ ምላስ አውለበለቡ።
ከከንፈራቸው በታች የእፉኝት መርዝ ነው።
አቤቱ ከኃጢአተኛ እጅ ጠበቀኝ።
እርምጃዬንም ሊያሰናክሉ ከመከሩ ከዓመፀኞች አድነኝ።
ትዕቢተኞች ወጥመድ ሰወሩብኝ።
ለእግሮቼም የወጥመድ ገመድን ዘረጉ ።
በመንገድ እንቅፋትን አኖሩ ።
እግዚአብሔርንም አንተ አምላኬ ነህ የልመናዬን ቃል አቤቱ አድምጥ አልሁት።
አቤቱ ጌታዬ የመድኃኒቴ ጉልበት

በሰልፍ ቀን ራሴን ሸፈንህ።
አቤቱ ለኃጢአተኞች ምኞት አትስጠኝ።
በላዬ ተማክሩ እንዳይጓደዱ አትተወኝ።
የሚከቡኝን ራስ የከንፈራቸው ክፋት ይክደናቸው።
የእሳት ፍም በላያቸው ይውደቅ።
እንዳይነሡም ወደ እሳትና ወደ ማዕበል ይጣሉ
ተናጋሪ ሰው በምድር ውስጥ አይጸናም።
ዓመፀኛን ሰው ክፋት ለጥፋት ይፈልጣዋል።
እግዚአብሔር ለችግረኛ ፍርድን ለድኃም በቀልን እንዲያደርግ አወቅሁ።
ጻድቃንም በእውነት ስምህን ያመሰግናሉ
ቅኖችም በፊትህ ይኖራሉ።

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ እስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን።